# እንዳይሆን

ገለባ ከምሮ _ ከሳት ፊት ወላፈን
ቃጠሎን በነፋስ _ አፍኖ ማዳፈን
ታይቶ አያውቅ ነገር _በበርኖስ ላይ ከፈን
ደስታ አይሉት መርዶ _ በሃዘን ቤት ዘፈን
እየሳቁ እለቅሶ _ ሙሾ ላይ እስክስታ
ጋብቻ ፈፅሞ _ ክህደት ካመኔታ
ጫጉላ ቤት ሠርገኛ _ በልጥ ተገንዞ
ቡራኬ ነው ፍታት? _እስስት መስቀል ይዞ?
እንዳይሆን እንዳይሆን _ ከመርሻ ጋር ጉዞ።

ግንቦት 2001